# የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥንምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ አባባ

ኢትዮጵያ

# የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

አዘጋጆች


ዶ/ር እሱባለው ጌታቸው (ጂማ ዩኒቨርሲቲ)

ዶ/ር አስናቀች ቱፋ (ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ)


አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኒላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ


© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

## ማውጫ

መግቢያ ........ 6
የሞጁሉ ጥቅል አላማ ........ 8
የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 8
የሞጁሉ ይዘቶች........ 8
የሞጁሉ የአቀራረብ ስልቶች ........ 9
ስልጠናው የሚወስደዉ ጊዜ ........ 10
ለስልጠናው የሚያመሰፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች፡- ........ 10
ማጠቃለያ ........ 10
ራስን መገምገሚያ ቼክሊስት ........ 10
ምዕራፍ አንድ፡-የሙስና ወንጀል ምንነት........ 11
1.1 መግቢያ ........ 11
1.2 የምእራፉ ዓላማ........ 11
1.3 የተፈቀደው ሰዓት........ 11
1.4 የምዕራፉ ይዘቶች........ 11
1.5 የማነቃቂያ ጥያቄዎች........ 11
1.6 የሙስና ወንጀል ምንነት........ 12
1.7 የሙስና ዓይነቶች........ 14
1.7.1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption) ........ 14
1.7.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)........ 15
1.7.3. ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)........ 16
1.7.4. ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)........ 16
1.8 የሙስና ወንጀል ምንነት........ 18
1.9 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት........ 19
1.9.1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት........ 19
1.9.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት ........ 20
1.9.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም ........ 20
1.9.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር........ 20
1.9.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ........ 21
1.10 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ........ 21

ምዕራፍ ሁለት፡ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ........ 30
2.1 መግቢያ ........ 30
2.2 የምዕራፉ አላማ ........ 30
2.3 የተፈቀደው ሰዓት ........ 31
2.4 የምዕራፉ ይዘቶች ........ 31
2.5 የማነቃቂያ ጥያቄዎች (Brainstorming) ........ 31
2.6 የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሁናዊ ገፅታ ........ 31
2.7 ሙስና በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ........ 34
2.7.1 የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እና ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮች. 34
ምዕራፍ ሶስት፡ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶች ........ 44
3.1 መግቢያ ........ 44
3.2 የምዕራፉ ዓላማ ........ 44
3.3 ስልጠናው የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ፤ ........ 45
3.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች ........ 45
3.6 በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚፈፀሙ ሙስና የመከላከያ ስልቶች ........ 49
3.6.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት ........ 49
3.6.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን ........ 49
➢ ግልጽነት ........ 49
➢ ተጠያቂነት ........ 50
3.6.3 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ ........ 51
3.6.4 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ ........ 51
3.6.5 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል ........ 52
3.6.6 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ ........ 53
3.6.7 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር ........ 53
3.6.8 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት ........ 54
3.6.9 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል ........ 55
ማጠቃለያ........ 60
ራስን መገምገሚያ ቼክሊስት ........ 61
ዋቢ መፅሃፍት(ማጣቀሻዎች)........ 63

## መግቢያ

ግብርና ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለምግብ ዋስትና ወሳኝ በሆነባት አገር የውሃ ሀብትን በመምራትና ዘላቂ የግብርና አሰራሮችን በማስተዋወቅ የመስኖና ቆላማ ሚኒስቴር አካባባቢ መስሪያ ቤት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በአየር ንብረት ልዩነት እና በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የተቀላጠፈ የመስኖ ስርዓት ፍላጎት እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትልቅ ፈተናዎች እና እድሎች አጋጥሞታል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለይ በቆላማ የሃገሪቱ አካባቢዎች የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ ወሳኝ የሆኑ የመስኖ መሰረተ ልማቶችን አያያዝ የመቆጣጠር ኃላፊነት፣የውሃ አጠቃቀምን ውጤታማነት እና የሰብል ምርትን ለማሻሻል የላቀ የመስኖ ቴክኒኮችን መተግበር፣የግብርና ምርትን ከፍ በማድረግ ሥነ-ምህዳሮችን የሚከላከሉ እና የሚያድሱ አሰራሮችን ማሳደግ እና የመሳሰሉት ሃላፊነቶች ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ዘርፍ የወሳኝ ውሃ ሀብት አስተዳዳሪ እንደመሆኑ መጠን የመስኖ ፕሮጀክቶች ግልጽና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ቁልፍ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ነገር ግን እንደ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋዋም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ለምሳሌ እንደ ጉቦ፣የገንዘብ አላግባብ አመዳደብ እና ፕሮጀክቶችን ለዘመድ አዝማድ የመስጠትና እና በመሳሰሉት ተግባራት ሊፈተን ይችላል፡፡ ሙስና የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ የውሃ አያያዝን ለማጎልበት እና የገጠር ልማትን ለመደገፍ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን ታማኝነት ሊያዳክም ይችላል፡፡ የህዝብ ሀብት ለግል ጥቅም ሲውል የመሠረተ ልማት ጥራት ይጎዳል፣ ማህበረሰቡም አስፈላጊ አገልግሎቶችን ያጣል፡፡ ይህም የኢኮኖሚ እድገትን ከማደናቀፍ ባለፈ ህዝቡ በመንግስት ተቋማት ላይ ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው፡፡

ስለሆነም በመስኖ እና በቆላማ አከባቢ ዘርፍ የስነምግባር ችግሮችን፣ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ ታስቦ ይህ ሞጁል በፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተዘጋጅቷል፡፡ ሞጁሉም በምዕራፍ አንድ ሙስና እና የሙስና ወንጀል ምንነት ይዳስሳል፣ በምዕራፍ ሁለት ሙስና በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲያተኩር በምዕራፍ ሦስት ደግሞ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችን የሚቃኝ ይሆናል፡፡

ይህ ሞጁል በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር መስሪያ ቤት ሙስናን በመለየት እና በመታገል የመስኖ አና ሌሎች ፕሮጀክቶች የታለመላቸውን አላማ እንዲያሳኩ በማድረግ የግብርና

ምርታማነትን ለማሳደግ እና የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል በተሻለ ሁኔታ የሚመለከተው የዘርፉ አካላት ሁሉ ሙስናን ለመዋጋት ትጥቃቸውን በመታጠቅ በጋራ የበለጠ ሥነ ምግባራዊ እና ውጤታማ የውሃ ሀብትን ለማስተዳደር መስራት የሚያስችል አቅም፣ ክህሎትን እና አመለካከትን ይገነባል።

ስለዚህ ኮሚሽኑ የሙስና እና የስነምግባር ማሰልጠኛ ሞጁሉን በውጤታማነት በመጠቀም የዘርፉን ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች እንዲሁም ሰራተኞች የሥልጠናው ዋና ተተኳሪዎች መሆናቸውን በመገንዘብ ስልጠናው ቀጣይነት ያለው የመማር፣ የመላመድ እና የማህበረሰብ ተሳትፎን የሚያጎላ የተቀናጀ አካሄድ በመከተል ውጤታማ ሊሆን ይችላል። የሙስናና የስነምግባር ማሰልጠኛ ሞጁሉን ተግባራዊ ማድረግ የመስኖና ቆላማ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤትን ታማኝነት እና ውጤታማነት በከፍተኛ ደረጃ ሊያሳድግ የሚችል ስትራቴጂያዊ ተነሳሽነት በመሆኑ የተቀናጀ አሰራርን በመከተል ሰራተኞችን በማሳተፍ እና የተጠያቂነት ባህልን በማጎልበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሙስናን በተሻለ ሁኔታ በመታገል በሁሉም የስራ ዘርፎች የስነምግባር ስራዎችን ማሳደግ እንዲችልና ሃብቶችን በዘላቂነት በማልማት የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱንም ሆነ የሚያገለግለውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ያደርጋል።

ስለሆነም የስልጠና ሞጁሉን በብቃት ለማድረስ የተለያዩ አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ተሳታፊዎችን ለማሳተፍ፣እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና አመለካከታቸውን ለማጎልበት የሚከተሉት የስልጠና ስልቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡- የማነቃቂያ ሃሳብ (Brainstorming)፣ ገለፃ (Presentation)፣ የቡድን ውይይቶች (Group discussions)፡ ልምድ መጋራት (Experience sharing)፡ አስረጂ ናሙናዎች (Case studies) እና ምላሽ እና ግምገማ (Feed-back and evaluation) ናቸው። ስልጠናውን ለማጠናቀቅም 3 የስራ ቀናት ወይም 12 ሰዓት ያስፈልጋል። ስልጠናውን ለማሳለጥም ፓወር ፖይንት፣ ማርከር፣ ፌሊፕ ቻርት፣ ስትከር ኖት፣ነጭ ወረቀት እና ወዘተ መርጃ መሳሪዎች አስፈላጊ ናቸው። በመጨረሻም ይህን ሞጁል የሚያስለጥኑ አሰልጣኞች ስለመስኖ፣ ስለግብርና፣ በሐገሪቱ ውስጥ ስላሉ ቆላማ አካባቢዎች እንዲሁም ስለመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር መ/ቤት፣ስለ ሙስናና ብላሹ አሰራሮችና ጉዳታቸውን በተመለከተ ቅድመ ግንዛቤ ቢኖራቸው የበለጠ ውጤታማ ይሆናል።

## የሞጁሉ ጥቅል አላማ

የዚህ ሞጁል ዋና አላማ ሰልጣኞች መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ለሙስና በጣም ተጋላጭ የሆነ ዘርፍ መሆኑን ተገንዝበው፣ በዘርፉ የሚፈጸመው ሙስናም በዜጎችና በሃገር ላይ የሚያደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት በመገንዘብ ሙስናን ለመዋጋት አስፈላጊውን እውቀት፣ክህሎት እና አመለካከትን በማዳበር በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ሥነ ምግባራዊ አሰራርን በማስፈን በተቋማቸው የሚፈጸመውን የአሰራር ሂደቶችን ከሙስናና ብልሹ አሰራር የጸዱ በማድረግ የራሳቸውን ሀላፊነት እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡

## የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች

ተሳታፊዎቹ በሚገባ ስልጠናውን ተከታትለው ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- የሙስና እና የሙስና ወንጀሎች ምንነትን ይረዳሉ፣
- መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከሰት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይለያሉ፣ይገመግማሉ፣
- በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያመጡ ጉዳቶችን ይለያሉ፣
- ሙስናን እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የራሳቸውን ሚና ይወጣሉ፣
- ሙስናን እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ረገድ ንቁ እርምጃዎች እንዲወስዱ በማድረግ፣ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት አሰራሮች ለግብርና ምርታማነት እና ለህብረተሰቡ ደህንነት አወንታዊ አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው የሚያስችል አቅምን ይፈጥራሉ፡፡

## የሞጁሉ ይዘቶች

### ምዕራፍ አንድ፡- የሙስና ወንጀል ምንነት

- ✓ መግቢያ
- ✓ የሙስና ምንነት
- ✓ የሙስና ዓይነቶች
- ✓ አስረጂ ናሙና
- ✓ የሙስና ወንጀል ምንነት

- ✓ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች
- ✓ የማጠቃለያ ጥያቄዎች እና ሃሳብ

**ምዕራፍ ሁለት፡- ሙስና በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ**

- ✓ መግቢያ
- ✓ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሁናዊ ገፅታ
- ✓ የሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮች በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እና ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች
- ✓ የማጠቃለያ ጥያቄዎች እና ሃሳብ

**ምዕራፍ ሶስት፡-በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚፈፀሙ ሙስና የመከላከያ ስልቶች**

- ✓ መግቢያ
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የመከላከያ ስልቶች
- ✓ መልመጃ
- ✓ የማጠቃለያ ሃሳብ

## የሞጁሉ የአቀራረብ ስልቶች

በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የተመለከተ የስልጠና ሞጁሉን በብቃት ለማድረስ የተለያዩ አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም ተሳታፊዎችን ለማሳተፍ፣እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና አመለካከታቸውን ለማጎልበት የሚከተሉት የስልጠና ስልቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

- ➢ የማነቃቂያ ሃሳብ (Brainstorming)
- ➢ ገለፃ (Presentation)
- ➢ የቡድን ውይይቶች (Group discussions)
- ➢ ልምድ መጋራት (Experience sharing)

- አስረጂ ናሙናዎች (Case studies)
- ምላሽ እና ግምገማ(Feed-back and evaluation)

**ስልጠናው የሚወስደዉ ጊዜ** ፦ 2 ቀናት/12 ሰዓት

**ለስልጠናው የሚያመሰፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች፡-** ላፕቶፕ፣ኤሊሲዲ፣ፓወር ፖይንት፣ ማርከር፣ ፊሉፕ ቻርት፣ ስትከር ኖት፣ነጭ ወረቀት እና ወዘተ...

**ማጠቃለያ**

**ራስን መገምገሚያ ቼክሊስት**

# ምዕራፍ አንድ፡- የሙስና ወንጀል ምንነት

## 1.1 መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው። ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል። በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው።

## 1.2 የምእራፉ ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

## 1.3 የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4፤00 ሰዓት

## 1.4 የምዕራፉ ይዘቶች

- ✓ የሙስና ምንነት
- ✓ የሙስና ዓይነቶች
- ✓ የሙስና ወንጀል ምንነት
- ✓ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

## 1.5 የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።

## 1.6 የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመስጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡
ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል" የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ "... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች

ይጨምራል…" በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር።

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል። የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችሰ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን። ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ።

በዚህም መሰርት ሙስና "Corruption" የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዘቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሕግ ትርጉም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የተባለ ተቋም "ሙስና" የሚለዉን ቃል ሲፈታዉ እንዲህ ይላል። Corruption is Defined as "Misuse of Entrusted Power for Private Gain." በዚህ ትርጉም መሰረት "ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል" ነዉ የሚል ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ በመገልግል ጉዳይን አላግባብ ማጓተት ወይም አላግባብ ፈቃድ በመስጠትና በማጽደቅ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል በሙስና ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይገልጻል። According to UNDP defined corruption as: the misuse of public power, office or authority for private benefit — through bribery, extortion, influence peddling, nepotism, fraud, speed money or embezzlement. በዚህ ትርጉም መሰረት "ሙስና ማለት የመንግስት ስልጣንን፣ የቢሮን ስልጣንን ለግል ጥቅም አላግባብ መጠቀም - በጉቦ ፣ በብዝበዛ ፣ በተፅዕኖ በመሸጥ ፣ በዘመድ አዝማድ ፣ በማጭበርበር ፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወይም ምዝበራ ማለት ነው። According to The African Union Convention on Preventing and Combating Corruption (AUCPCC) defines corruption as any acts or practices that are prohibited by the convention, including related offenses. በዚህ ትርጉም

መሰረት “ሙስና ማለት በኮንቬንሽኑ የተከለከሉ ተግባራት ወይም ተግባራት ተያያዥ ወንጀሎችን ጨምሮ እንደሆነ ይገልፃል”::

## 1.7 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፈላል፡፡

### 1.7.1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ የጥቃቅን ወይም አነስተኛ ሙስና መገለጫዎች እና ተፅዕኖዎች እንደሚከተሉት ይገለፃሉ፡፡

- ✓ የአካባቢው ባለስልጣናት የመስኖ አገልግሎት ወይም መሬት ለማግኘት ከገበሬዎች ወይም ሰራተኞች ጉቦ ሊጠይቁ ይችላሉ፣
- ✓ ባለሥልጣናት ለግብርና ሥራ አስፈላጊ ለሆኑ ፈቃዶች መደበኛ ያልሆነ ክፍያን መጠየቅ፣
- ✓ ባለስልጣናት የለፕሮጀክት ጥቅማጥቅሞች ለጓደኞቻቸው ወይም ለቤተሰብ አባላት ቅድሚያ መስጠት ለምሳሌ የመስኖ መሠረተ ልማት ወይም የገንዘብ ድጋፍ፡፡
- ✓ በመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚሰሩ ስራዎች ከጥቅም ይልቅ በግላዊ ግንኙነቶች ላይ ተመስርተው ለግለሰቦች ሊሰጡ ይችላሉ፣
- ✓ ተቋራጮች የፕሮጀክት ወጪን ከፍ በመድረግ ትርፉን ከሙስና ባለስልጣኖች ጋር በመጋራት የስራ ጥራት እንዲቀንስ ማድረግ፣
- ✓ ርካሽና ዝቅተኛ ጥራት ያላቸውን የመስኖ ፕሮጀክቶችን ለማጽደቅ ጉቦ መቀበል፣
- ✓ ጉቦ እስካልተከፈለ ድረስ አገልግሎቶችን ወይም ድጋፎችን መከልከል እና የሳሰሉት ናቸው፡፡

### 1.7.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሸሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 " ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

በመስኖ እና የቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ መጠነሰፊ ሙስና በሚከተሉት ተግባራቶች ሊገለፅይችላል፡፡

- ለዋና የመስኖ ፕሮጀክቶች የታቀዱ ከፍተኛ ገንዘቦች ለታለመለት አላማ ያለመዋል፣
- ለመስኖ መሠረተ ልማት ኮንትራቶች የተጋነኑ ክፍያዎችን መጠየቅ፣

- ከፍተኛ ባለስልጣኖች ለልማት የታሰቡ ገንዘቦችን በማጭበርበር ሌላ ወይም አስፈላጊ ያልሆኑ ፕሮጀክቶችን ማጽደቅ ፣
- ባለሥልጣናቱ ከኮንትራክተሮች ጋር ብልሹ የሆነ ስምምነቶችን ሲያደርጉ፣ ትርፋማ ኮንትራቶችን በመስጠት ምትክ በመቀበል፣
- በሙስና ፕሮጀክቶች ውስጥ ያሉ ቁልፍ የስራ መደቦች ብቃታቸው ምንም ይሁን ምን በዘመዶች ወይም በጓደኞች ጓደኞች ሲሞሉ፣
- ለሙስና ፕሮጀክቶች የሚውለው ገንዘብ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ጥቅም ላይ ሲውሉ፣
- ዋና ዋና የሙስና ፕሮጀክቶች ሊቆሙ ወይም በአግባቡ ሳይከናወኑ መቅረት ወይም መዘግየት እና በማሳሰሉት ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ የዋልታቲቪ፡https: //www. youtube.com/ watch?v=cWJyFM8I08o፣ የሪፖርተር ጋዜጣ፡https://www.ethiopianreporter.com/129149/)

### 1.7.3. **ፖለቲካዊ ሙስና** (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲን እና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

### 1.7.4. **ስርዓታዊ ሙስና** (systemic capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡

ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture ) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

**አስረጂ ናሙና 1፡ የሙስና አይነቶች በተቋም ደረጃ**

ሮበርት ዋድ (1982) የተባለው ፀሐፊ በደቡባዊ ህንድ ስለተከሰተ ሰፊ የመስኖ ልማት ተቋማዊ ሙስና በዝርዝር አቅርቧል፡፡ የፕሮጀክት ባንክ ሂሳቡ የተከፈተው እንደ ኢውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1982 ነው፡፡ ነገር ግን በ"ሃይድሮሊክ ቢሮክራሲ" ውስጥ የአስተዳደር እና የፖለቲካ ሙስና ስርዓትን የሚቆጣጠሩ መደበኛ ያልሆኑ ደንቦች በዝርዝር የተሰጠ መግለጫ ነው:: ነገር ግን ደራሲው በህንድ ውስጥ በመስኖ ዘርፍ ስላለው ትክክለኛ አሠራር ምንም መረጃ የለውም፡፡

ፀሐፊው ባለስልጣናት ከፍተኛ የማመዛዘን ችሎታ እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ የግንባታ ድረጅቶች በግንባታ ኮንትራት ውል ለማግኘት ፈልገው የግንባታ ፍቃድ ማግኘት ችለዋል፣ በዚህም ከእያንዳንዱ ውል ዋጋ ቢያንስ 16 በመቶ ለአስፈፃሚ ባለስልጣናት የሚውል ነው:: በተጨማሪም በግንባታው ወቅት ዝቅተኛ ጥራት ያለው እና አነስተኛ ስራን በመፍቀድ እስከ 50 በመቶ የሚሆነውን የኮንትራት ዋጋ ይወጣል፡፡ ህገ-ወጥ ገንቢዎቹ በኮንትራክተሮች እና ባለስልጣናት በጋራ በመመሳጠር በዓመት 3,500 የአሜሪካ ዶላር የሚደርስ ኦፊሻል ደመወዝ ያለው የሥራ አስፈፃሚ መሐንዲስ ከግንባታ ሥራ 32,000 የአሜሪካ ዶላር ሕገ-ወጥ ገቢ ያገኝ ነበር፡፡ የመስኖ ግንባታ ተጠቃሚ ገበሬዎች ጉቦ በመስጠት መስኖ ለማግኘት ወደ 3,000 የአሜሪካ ዶላር ለውሃ አቅርቦት ይከፍላል፡፡ የግንባታ ድረጅቶች በየሶስት አመቱ አዳዲስ መሀንዲሶች ይተላለፉ ነበር፣ እና ተመራጭ የስራ ቦታ ለማግኘት መሐንዲሶቹ ከ12,000 እስከ 50,000 የአሜሪካ ዶላር መካከል ለግዛቱ የመስኖ ሚኒስትር ተወካይ በሙስና መልክ ይከፍላሉ፡፡ በዚህ ከደቡብ ሕንድ የመጣ ምሳሌ፣ ጥቃቅን ሙስና የሙስና 'ፒራሚድ' መሠረት ይመሰርታል፡፡ እንደማሳያም ጉቦ እና ከሽርክና የሚገኘው ገቢ ጥቅም ለዘርፉ ተዋንያን በተዋረድ ተይዛል፡፡ በመሆኑም ሙስናውን ወይም ጉቦውን ለሥራው መክፈል ያልፈለገ መሐንዲስ ተቆጥሮ የመቀጠር ዕድል የለውም፡፡ በተጨማሪም ህጉን ተከትሎ እና ሐቀኛ መሐንዲስን ከሥልጣኑ ለማንሳት በሕዝብ ፊት በሙስና ወንጀል ይከሱታል፡፡

**Source (ምንጭ):** UNDP, 2011, Fighting Corruption in the Water Sector Methods, Tools and Good Practices, New York, NY 10017, USA.

***የመወያያ ጥያቄዎች***

<u>ከላይ ያለውን አስረጂ ናሙና አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኃላ በቡድናችሁ ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች ላይ በጥልቀት ከተወያያችሁ በኃላ ለተሳታፊዎቹ አቅርቡ።</u>

- ✓ ከአስረጂ ናሙናው ምን ተረዳችሁ? የሙስናውስ አይነት ከየትኛው የሙስና አይነት ይመደባል? ለምን?
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ እንደዚህ አይነት ሙስና አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካለ መገለጫዎቹስ ምን ምንድናቸው?
- ✓ እነደዚህ አይነት ሙስና ለመከላከል ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር ዘርፍ እንዲሁም ከእያንዳንዳችሁ ምን ይጠበቃል?

## 1.8 የሙስና ወንጀል ምንነት

የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፡-

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ  የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር።

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን  የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና

ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *"... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል..."* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

## 1.9 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡ የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

### 1.9.1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ፡፡ የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣

እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል፡፡

### 1.9.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል ፡፡ ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል፡፡ ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል፡፡ ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል፡፡

### 1.9.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.9.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ

ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.9.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመንዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሸጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኮን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.10 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

### 1.10.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም*

ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.10.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤ በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.10.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም፦ የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስና የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል።

### 1.10.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል። ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል። በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም።

### 1.10.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ

እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤ በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.10.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል።

### 1.10.17 ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል። በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ

ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ  ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.10.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.10.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.10.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.10.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ

ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣  ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡ ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ  ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

### 1.10.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.10.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

### 1.10.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

### 1.10.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. "ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት" በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል" ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

## የማጠቃለያ ሃሳብ

እንደአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

## 2.1 መግቢያ

ሙስና በተለያዩ ዘርፎች በተለይም በግብርናና በመስኖ ልማት የሚደረጉ ጅምሮችን ውጤታማነትና ዘላቂነት የሚያዳክም ሰፊ ጉዳይ ነው፡፡ ውጤታማ የውሃ አያያዝ እና የግብርና ምርታማነት ለምግብ ዋስትና እና ለኢኮኖሚያዊ መረጋጋት ወሳኝ በሆኑበት በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሙስና እድገትን በእጅጉ ሊያደናቅፍ እና ድህነትን ሊያባብስ ይችላሉ፡፡ ቆላማ አካባቢዎች ብዙ ጊዜ ለውጤታማ አስተዳደር የታለመ ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልጋቸው ልዩ የስነ-ምህዳር እና የግብርና ባህሪያት አሏቸው፡፡

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ግብርና የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት በሆነባቸው አካባቢዎች የመስኖ ልማትን ለማሳደግ የመስኖ ስራ አስፈላጊና መሰረታዊ ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን የመስኖ ፕሮጀክቶችን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር በተለያዩ ብልሹ አሰራሮች ሊሰናከሉ ይችላሉ፡፡ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሙስና በተለያዩ መንገዶች ሊከሰቱ ይችላል፡ ለምሳሌ ባለሥልጣናቱ ኮንትራቶችን ለማስጠበቅ ወይም ፈቃዳቸውን ለማፋጠን ከኮንትራክተሮች ወይም አቅራቢዎች ጉቦ መቀበል ይችላሉ፣የግዥ ሂደቶችን መጠቀሚያ ውል ላልሆኑ ወይም ጨዋነት የጎደላቸው አቅራቢዎች ውል እንዲሰጥ ማድረግ፣ለመስኖ ፕሮጀክቶች የታቀዱ ገንዘቦች ለግል ጥቅም ማዋል፣የወዳጆች ወይም የቤተሰብ አባላትን መቅጠርና በመሳሰሉት መልኩ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር ያለው ሙስና ለዘላቂ ልማትና ለምግብ ዋስትና ትልቅ ፈተና ስለሚሆን የሙስናን ምንነት እና ተፅእኖ በመረዳት ባለድርሻ አካላት በትብብር ታማኝነትን፣ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን በማጎልበት በመስኖ ስራዎች ላይ ጥገኛ የሆኑትን ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

## 2.2 የምዕራፉ አላማ

ከስልጠናው በኃላ ሰልጣኞች፡-

- የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ለሙስና ያለው ተጋላጭነትን ይረዳሉ፣ያብራራሉ፣

- የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት በሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚመጡ ጉዳቶችን ይረዳሉ፣ይለያሉ፣
- በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ለሚስተዋሉ የፕሮጀክት መጓጓተት ምክንያቶችን ይለያሉ፡፡

## 2.3 የተፈቀደው ሰዓት

5 ሰዓት

## 2.4 የምዕራፉ ይዘቶች

- **የሙስና ወንጀሎች** በበመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት
  - ✓ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር መ/ቤት ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እና ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች

## 2.5 የማነቃቂያ ጥያቄዎች (Brainstorming)

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ ተወያዩባቸው እና የደረሳችሁበትን ለተሳታፍዎች አጋሩ፡፡</u>

1. በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር መ/ቤት ወቅታዊ አሰራር ላይ ምን አይነት የሙስና ተጋላጭነቶችን ይመለከታሉ?
2. በመስኖ እና በቆላማ አካባቢ የልማት ፕሮጀክቶች ምን አይነት ሙስና ታዝባቹሃል?
3. በተመሳሳዩ አውዶች ውስጥ ተጋላጭነትን የቀነሱ የተሳካላቸው ተነሳሽነቶች ምሳሌዎችን ማጋራት ይችላሉ?
4. በዘርፉ ለሚስተዋሉ የፕሮጀክቶች መዘግየት/መጓተት ምክንያቶቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 2.6 የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሁናዊ ገፅታ

በኢትዮጵያ ከትላልቅ እስከ መካከለኛ እርሻዎችን ለማልማት መስኖ ጥቅም ላይ ሲውል ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ለአገሪቱ የግብርና ዘርፍ እና አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ከሚፈጥረው ዕድል አንፃር ሲታይ አሁንም የሚጠበቀውን ያህል ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡

በተጨማሪም ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2023 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ባስቀመጠችው ግብ መሰረት የተፈጥሮ ሀብትና የመስኖ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም ይህንን ራዕይ እውን ለማድረግ ያስችላታል።

ይህ ራዕይ እውን እንዲሆን ሊፈታ የሚገባው ወሳኝ ጥያቄ የምግብ ዋስትና እና የአየር ንብረት መለዋወጥን የመቋቋም ጥያቄ ነው። የመስኖ ቴክኖሎጂ ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋለ ይህን ችግር ለመፍታት የሚረዳና በሌሎችም ዘርፎች አዎንታዊ ውጤት ሊኖረው የሚችል አማራጭ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጥያቄ በአገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ከሚገኙ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ጋር የተያያዘ ነው። የኢትዮጵያ ቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች ሊሰጡ የሚችሉት ጥቅምና ዕድሎች በመጠን ብዙ ቢሆኑም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጥልቀት ተመርምረው ያልሰፈሩ ናቸው።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች የሚገኘውን ሰፊ መሬት፣ ውሃ፣ እንስሳትና የሰው ሀብት በመጠቀም አገሪቱ የልማት ተልዕኮዋን እንድታሳካ የኢትዮጵያ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ተቋቋመ።

**የሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ራእይ**

በሳይንሳዊ ምርምር የተደገፈ፣ ለአየር ንብረት መለወጥ የማይበገር የመስኖ ልማትን በመተግበር የምግብ ሉአላዊነትንና ዋስትናን በማረጋገጥ እንዲሁም የቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማትና አስተዳደርን በማጠንከር የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት ነው።

**የሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ተልዕኮ**

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተልዕኮ ዘመናዊ የመስኖ ስርዓትን በመተግበር እና ድርቅን የመቋቋም አቅምን በማጎልበት ለቆላማው የኢትዮጵያ ክፍል ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለውን ራዕይ ማሳካት ነው። እንዲሁም የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህልውና በማያናጋ መልኩ ውሃን እንደ ቁልፍ ሃብትና ግብአት በመጠቀም ሁለንተናዊና የተቀናጀ ዘላቂ ልማትና አስተዳደርን ለማስፈን ሚኒስቴሩ ተግቶ ይሰራል።

**የሚኒስተር መስሪያ ቤቱ መመሪያ**

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት በአዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት መዋቅር በአዋጅ ቁ. 1263/2021 መሰረት የተቋቋመ አዲስ ሚኒስቴር ነው፡፡ ሚኒስቴሩ የተቋቋመው በውሃ-ኢነርጂ መሠረተ ልማቶች መካከል የነበረውን ክፍተት ለማጥበብ እና አስፈላጊውን የግብርና ምርታማነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም በመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ዘላቂ ልማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የምግብ ሉዓላዊነትን፣ የምግብ ዋስትናና የኑሮ መሻሻልን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት መስኖ እንዲሁም የቆላማ አካባቢዎች ልማትና አስተዳደር ወደ ሚኒስቴር ተቋምነት አድገዋል፡፡

**የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መመሪያ ነባራዊ ሁኔታ**

መንግስት ባደረገው የሴክተር መ/ቤቶች አስፈጻሚ አካላትን በአዲስ መልክ እንዲደራጁ ባደረገው መሠረት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 በአዲስ መልክ በሚ/ር መ/ቤት ደረጃ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት በመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ በሰላም ሚኒስቴር የፌደራሊዝምና አርብቶ አደር ልማት ዘርፍ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ጋር የተያያዙ እና በሌሎች አካላት ይከናወኑ የነበሩ ተግባራት ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒሰቴር እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

ሚ/ር መ/ቤቱም ከተሰጡት ተግባራትና ሃላፊነቶች መካከል በዋናነት የመስኖ ልማትን በማስፋፋት እና በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶችን ግንባታ በወቅቱ በማጠናቀቅና ወደ ልማት በማስገባት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ የኑሮ ሁኔታቸውን ማሻሻል ዋናዎቹ ናቸው፡፡በዚህም መሠረት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ባሉባቸው ክልሎች በዕቅድ ተይዘዋል፡፡

አሁኑ ውቅት አፋር፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ኦሮሚያ ክልል፣ ደቡብ ኢትዮጵያ, ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ, በመካከለኛው ኢትዮጵያና ዋግሀምራ ዞን በተለያዩ ዘርፎች በርካታ የግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታዎች በመገንባት ላይ የሚገኝ ሲሆን ግንባታዎች ሲጠናቀቁም ለአርሶ እና አርብቶ አድሩ ህይወት በመቀየር እና ሐገራችን

ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን ለማረጋገጥ ለምታደርገው ጥረት ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡(MILLs https://www.mills.gov.et/am-et/)

## 2.7 ሙስና በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ ያለው ሙስና የፐብሊክ ሰርቪሱን ታማኝነት እና ውጤታማነት የሚጎዳ ከውሃ አስተዳደር፣ከፕሮጀክቶች መዘግየት እና ከግብርና ልማቶች ጋር የተያያዙ ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ያመለክታል፡፡ በመስኖ እና በቆላማ አከባቢ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና በግብርና ምርታማነት፣በውሃ አያያዝ እና በገጠር አኗኗር ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ቁልፍ ነጥቦች፡- የበጀት አጠቃቀምና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም፣የፕሮጀክቶች መጓጓተት፣የግብዓት አቀራረብና ስርጭት፣የሀብት አመዳደብና አጠቃቀም እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ (በኮሚሽን መ/ቤቱ የተጠና የ2015 ጥናት)

### 2.7.1 የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እና ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮች

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ለሙስና ያለው ተጋላጭነት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ የሚችል ሲሆን የግብርና መስኖ ፕሮጀክቶችን እና የሀብት አጠቃቀምን ውጤታማነት ይጎዳል፣ የፕሮጀቶቶች መዘግየትንም ያስከትላል፡፡ የመስኖ እና ቆላማ ዘርፍ ለሙስና ተጋላጭ የሚሆንብት ምክንያቶች በርካታ ኢንቨስትመንቶች በመኖራቸው እና በትላልቅ የመስኖ መሠረተ ልማት ውስጥ ያሉ እንደ ግድቦች፣ቦዮች፣ ጉድጓዶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች እንዲሁም በትላልቅ ፕሮጀክቶች ውስጥ ብዙ ትናንሽ የመስኖ ስራዎች መከናወን፣የመስኖ ውሃ ቫልዩ እና ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም እና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡ስለሆነም የመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት በሚከተሉት ተያያዥ ምክንያቶች ለሙስና ሊጋለጥ ይችላል፡፡

#### 2.7.1.1. የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተበመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር የተስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች

በተለይም የውሃ እጥረት እና የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ተግዳሮቶችን በሚፈጥሩ ክልሎች የመስኖ እና የቆላማ አካባቢ ሃብቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መቆጣጠር ለግብርና ምርታማነት እና ለምግብ ዋስትና ወሳኝ ነው፡፡ ነገር ግን ለመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት

የተመደበው በጀት ለሙስና የተጋለጠ ከሆነ የልማት ጥረቱን የሚያዳክም እና ድህነትን የሚያባብስ ይሆናል።

በዚህ ዘርፍ ያለው ሙስና በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡ እነዚህም የገንዘብ ምዝበራ፣ ጉቦ እና የግዥ ማጭበርበር ናቸው። እንደዚህ አይነት ብልሹ አሰራሮች ሃብቶችን ከመሠረታዊ ፕሮጀክቶች ከማራቅ ባለፈ ጥራትንና ዘላቂነትን ያበላሻል። ለምሳሌ ለመስኖ ልማት የታቀዱ ገንዘቦች ሊመዘበሩ ይችላሉ፣ ይህም የገበሬዎችን ፍላጎት ወደ ማያሟሉ ወይም ደረጃቸውን ያልጠበቁ ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ ያደርጋል።

እንደማሳያም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም 23ኛ መደበኛ ስብሰባውን ባካሄደበት ወቅት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤትን የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን አቅርቧል። በሪፖርቱም ሚኒስቴሩ የበጀት ዓመቱ ሲጀመር ተይዞለት ከነበረው 7.8 ቢሊዮን ብር በዘጠኝ ወራት ውስጥ 5.4 ቢሊዮን ብር ወጪ አድርጎ ሥራ ላይ ማዋሉን ተገልጿል። በተጨማሪም ባለፈው ዓመት ከተጠናቀቁ ሦስት ፕሮጀክቶች ውጭ፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አንድም ፕሮጀክት በዕቅዱ መሠረት ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ አለመኖሩን ገልፀው ከታቀዱት 10 ፕሮጀክቶች የሥራዎች አፈጻጸማቸው ዜሮ በመቶ፣ 17 ሥራዎች ደግሞ ከ50 በመቶ በታች ሆነው እያለ 5.4 ቢሊዮን ብር ክፍያ መፈጸሙ በቋሚ ኮሚቴው ቅሬታን አስነስቷል።

ቋሚ ኮሚቴው በክልሎች መካከል ያለው የአፈጻጸም ግምገማ ሰፊ ልዩነት ማሳየቱ የሚኒስቴሩን ድጋፍና ክትትል መላላት የሚያሳይ ነው ሲል የገለጸ ሲሆን፣ በደቡብ ክልል ውስጥ ሲከናወኑ የነበሩ ፕሮጀክቶች በክልሉ እንደ አዲስ መደራጀት ምክንያት ፕሮጀክቶቹ ተጓተዋል በሚል በምክንያትነት የተቀመጠው ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ፣ የሚኒስቴሩ ድጋፍና ክትትልን መላላት የሚያሳይ ነው በማለት አስቀምጧል፡

በመጨረሻም የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሚኒስቴሩ በቋሚ ኮሚቴው የሚሰጡ አስተያየቶችን እየተቀበለ አለመሆኑን ገልጸው፣ የበጀት አጠቃቀሙ ለሙስና ተጋላጭ እየሆነ ነው ብለዋል። አክለውም ዕቅድና ሪፖርቱ መሬት ላይ ካለው ሁኔታ አንፃር አለመናበብ መኖሩን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም የ2015 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በቀን 27/12/2014 በኢንቮይስ ቁጥር 12101 ለአለማየሁ ከተማ ጠቅላላ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ

የግንባታ መያዣ ክፍያ ብር 44,755,532.47 ተመላሽ ሲደረግ የመያዣ ተከፋይ በሂሳብ መደብ 6175101 (5061) በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2311208 (6324) የግንባታ ሥራ ክፍያ ያለአግባብ በወጪ መመዝገቡ፣ በሂሳብ መደብ 6172202 (ልዩ ልዩ ተከፋይ) ብር 499,530,003.97 እና በሂሳብ መደብ 6175101(የግንባታ ሥራ መያዣ ተከፋይ ብር 1,048,356,586.26 በድምሩ ብር 1,547,886,590.23 ተከፋይ ሂሳብ ማስረጃ የሌለውና ሂሳቡ ለማን እንደተከፈለ የማይታወቅ መሆኑ፣ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ሥልጠና እንዲሰጥ በታዘዘው ደብዳቤ ከተገለፀው ቀን በላይ የውሎ አበል ክፍያ በመፈፀሙ በድምሩ ብር 180,156.85 (481417.00-301260.15) በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፣በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 1,547,886,90.23 ሪፖርት የተደረገ ሲሆን ለማን የሚከፈልና የማይታወቅ እና ማስረጃ ያለቀረበለት መሆኑ፣ በድምሩ 1,159,744.53 ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ እና በድምሩ ብር 29,872,500.87 ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ያልተወራረደ(ያልተከፈለ) መሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤት የበጀት አጠቃቀም ለሙስና የተጋለጠ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን ይህ “ወድድሮች፣እና የመሣሰሉት የሙስና ወንጀሎች እንዲከሰቱ ያደርጋል፡፡

ስለሆነም እነዚህና የመሳሰሉት ደካማ የበጀት አጠቃቀሞች የገንዘብ መበዝበዝን፣ የተጭበረበሩ ኮንትራቶች፣የተጋነኑ ወጪዎች ወይም አቅም ለሌላቸው ወይም ብቁ ላልሆኑ ድርጅቶች ኮንትራቶችን መስጠት፣የማይገኙ/ያለተሰሩ ምናባዊ ፕሮጀክቶችን መፍጠር እና የመሣሠሉት የሙስና ወንጀሎች እንዲከሰቱ በር ሊከፍት ይችላል፡

### 2.7.1.2. የተሽከርካሪ አያያዝ እና አጠቃቀም በተመለከተ በመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር የተስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች

የመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ሃብቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መቆጣጠር ለግብርና ምርታማነት እና ለገጠር ልማት ወሳኝ ነው፡፡ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ ተሽከርካሪዎች ስራዎችን በማመቻቸት፣ፕሮጀክቶችን በመከታተል እና የመስክ ስራዎችን በመደገፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ነገር ግን የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም ለሙስና የተጋለጠ ከሆነ በሃብት ድልድል እና በፕሮጀክት ትግበራ ላይ ከፍተኛ አደጋን ይፈጥራል፡፡

በዚህ አውድ ውስጥ ያለው ሙስና በተለያዩ መንገዶችን ሊገለጥ ይችላል፣ እነዚህም ኦፊሴላዊ ተሽከርካሪዎችን ለግል ዓላማ አላግባብ መጠቀም፣ የተጭበረበረ ነዳጅ ደረሰኝ ይገባኛል ጥያቄ እና

የተሽከርካሪ ግዥ ሂደቶችን መጠቀምን ያጠቃልላል። እንደነዚህ ያሉት አሠራሮች ገንዘቦችን ከመስኖ ፕሮጀክቶች ላይ ከማስወገድ ባለፈ የአገልግሎት አሰጣጡን ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ይጎዳሉ። ለምሳሌ የመስኖ መሠረተ ልማትን ለመከታተል የታቀዱ ተሽከርካሪዎች ለግል ግልጋሎት ሲውሉ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንቅፋት ይፈጥራል፣ በመጨረሻም የምግብ ዋስትናን እና የግብርና ዘላቂነትን ይጎዳል።

እንደማሳያ የ2015 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች እንደሚያሚያሳዩት፦

- 1(አንድ) ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌለው መሆኑ፣
- የ23 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር(ሊብሬ) የተመዘገበው በሌላ መ/ቤቶች ስም መሆኑ፣
- የ16 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት የመታወቂያ ደብተር(ሊብሬ) በግለሰቦች ስም መሆኑ እና አገልግሎት የማይሰጡ 5 ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ያሳያል።

በመሆኑም እንደዚህ አይነት ብልሹ ተግባራት ተሽከርካሪዎችን አላግባብ መጠቀም፣በተሽከርካሪ ግዢዎች ላይ ሰጥቶ መቀበልን፣የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ያለፍቃድ ለግል እና ለቢሮ ስራዎች መጠቀም፣ለማይኖሩ ወይም አገልግሎት ላይ ላልሆኑ ተሽከርካሪዎች በጀት ማውጣት፣ ለተሽከርካሪ አገልግሎቶች ከመጠን በላይ ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ የገንዘብ ምዝበራን፣ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

### 2.7.1.3. ግዥን በተመለከተ በመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር የተስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች

በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የግዥ ሂደቶች የግብርና ምርታማነትን እና ዘላቂ የሀብት አያያዝን ለማሳደግ የታለሙ ፕሮጀክቶችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ወሳኝ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሂደቶች ብዙውን ጊዜ ለሙስና የተጋለጡ ናቸው። ይህም የህዝብ ወጪን ውጤታማነት በእጅጉ የሚጎዳ እና የልማት ግቦችን የሚያደናቅፍ ስሆን በግዥ ላይ የሚፈጸመው ሙስና በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡ ለምሳሌ ጉቦ፣ መማፀን እና የኮንትራት ሽልማቶችን በመጠቀም ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ፣ የተጋነነ ወጪ እና በመጨረሻም የአስፈላጊ ፕሮጀክቶች ውድመት ያስከትላል።

እንደማሳያም በፌዴራል ሥነ-መግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተደረገው በ2015 ጥናት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክት አፈፃፀም አከባቢ የተለዩ የሙስና ተጋላጭነቶች፡-

- የገንዘብ መጠናቸው በአንፃራዊ ከፍተኛ የሆነ ዕቃዎችን በውስን ጨረታ እንዲፈጸም መደረጉና በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ግዥዎች የተፈጸሙ መሆናቸው፤
- ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የገበያ ዋጋ ጥናት በማድረግ በተጋነነ ዋጋ ግዥ እንዳይፈጸም ለመከላከል ጥረት አለማድረግ፤
- ለመስኖ ግንባታ የሚሆኑ ግባአቶች ጥራታቸውን ያልጠበቁ እና ጥራት ያላቸው እቃዎች እንዲቀርቡ የክትትል ክፍትት መኖሩ፣
- በቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚበቅሉ ግባቶች ማለትም ምርጥ ዘር፣
- የእንሳስት ግባአቶች ጥራታቸውን ያልጠበቁ መሆን እና ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በሕግ ክፍል ተገቢው አስተያየት እንዲሰጣቸው ያለማድረግ እና የመሣሠሉት ሲሆኑ እነዚህ ብልሹ አሰራሮች ጉቦ መቀበልና መስጠትን፣አቅራቢዎች ዋጋን ለማስተካከል ወይም ጨረታዎችን ለማጭበርበር ማሴር፣
- ፍትሃዊ ውድድርን ማዳከም እና የተጋነነ ወጪዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 2.7.1.4. የፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ በመስኖ እና ቆላማው አካባቢ ሚኒስቴር የተስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች

በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በተሳካ ሁኔታ መተግበራቸው የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የተፈጥሮ ሀብትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ወሳኝ ሂደት ብዙውን ጊዜ ለሙስና የተጋለጠ ከሆነ የፕሮጀክቶችን ዓላማዎች ሊያበላሽ እና የህዝብ ገንዘብን ሊያባክን ይችላል፡፡ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የሚፈጸመው ሙስና ጉቦ፣ የተጭበረበረ ሪፖርት ማቅረብ፣ የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳዎችንና አተገባበርን መጨመር እና በመሳሰሉት መንገዶችን ሊገለጥ ይችላል፡፡ እነዚህ መሰል ተግባራት የገንዘብ ኪሳራ ከማስከተል ባለፈ አርሶ አደሩንና የገጠር ማህበረሰብን ለመደገፍ የታቀዱ መሠረተ ልማቶችን እና አገልግሎቶችን ጥራትና ውጤታማነት ይጎዳል፡፡

የፕሮጀክት ትግበራ በዚህ ዘርፍ ለሙስና ተጋላጭነት እንድኖረው በርካታ ምክንያቶች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ በቂ ያልሆነ የቁጥጥር እና የክትትል ዘዴዎች ብልሹ አሰራሮችን ያለ ቁጥጥር እንዲያብቡ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክት እቅድ ማውጣትና አፈጻጸም ላይ ግልጽነት

የጎደለው ተግባር ለሥነ ምግባር የጎደላቸው እንደ የተጋነነ ወጪ እና ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ ዕድሎችን ይፈጥራል። የፖለቲካ አድሎአዊነት ተጽእኖ የፕሮጀክቶችን ቅድሚያዎች ሊያዛባ ይችላል። በዚህም ምክንያት ከእውነተኛ የእድገት ፍላጎቶች ይልቅ በግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረተ የሃብት ድልድል እንዲፈጠር አስተዎፅዖ ሊያደርግ ይችላል።

እንደስጋትም በፌዴራል ሥነ-መግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተደረገው በ2015 ጥናት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጅክት አፈፃፀም አከባቢ የተለዩ የሙስና ተጋላጭነቶች፡-

- በሚኒስቴር መ/በቱ የሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች የግንባታ መጓተት፣

በመስኖ እና በቆላማ አካባቢዎች የፕሮጀክቶች ትግበራ መጓተት ብዙውን ጊዜ ከሙስና ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለውና በግብርና ምርታማነት እና በሀብት አያያዝ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው። ይህንን ግንኙነት መረዳቱ ለውጤታማነት እና የህዝብ አመኔታ ማጣት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን መሰረታዊ ጉዳዮች ለመፍታት ወሳኝ ነው።የፕሮጀክት የጊዜ ገደብ ሲራዘም ለሙስና ተጨማሪ እድሎችን ይፈጥራል። መዘግየቶች ክፍያን ለማስጠበቅ ወይም ለማፋጠን ከሚፈልጉ ተቋራጮች የጉቦ ጥያቄን ወይም ሰጥቶ መቀበልን ያስከትላል።የተራዘሙ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ወጪዎችን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ እነዚህም በማጭበርበር ዘዴዎች ሊከናወኑ ይችላሉ። የተራዘመው የጊዜ ሰሌዳ ፈንዶችን ለመሳብ ብዙ እድሎችን እንደሚፈቅድ በማወቅ ተቋራጮች ወጪን ሊጨምሩ ይችላሉ።

በተጨማሪም የፕሮጀክቶች መዘግየቶች ብዙውን ጊዜ ደካማ የቁጥጥር እና የክትትል ዘዴዎችን ያመለክታሉ። የፕሮጀክት ማኔጅመንት የላላ በሚሆንበት ጊዜ የኮንትራክተሮች አፈጻጸምና የሀብት ድልድል የመፈተሽ ሂደት አነስተኛ ስለሆነ ብልሹ አሰራሮች በቀላሉ ስር ሊሰዱዱ ይችላሉ።የዘገዩ ፕሮጀክቶች በቂ ያልሆነ ሪፖርት እና ሰነድ ስለማይኖራቸው ተጠያቂነትን ያደበዝዛሉ፣ግልጽነት በማጉደል ለሙስና አሰራርን ያመቻቻሉ (Wells,2015)።

በመሆኑም የፕጀክቶች መዘግየትን በተለከተ የመስኖና ቆላማ  ሚኒስቴር በፓርላማ የ2023/24 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በተያዘላቸው ጊዜ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ደካማ አፈጻጸምን አስመልክቶ በበፓርላማ አባላቶች የተገለጹትን ሥጋቶች አምነው የመስኖ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ለማስፈፀም በቂ የአገር ውስጥ ኮንትራክተሮች እንደሌሉ እና አቅማቸው በቂ አለመሆኑን ገልፀዋል። በቆላማ ክልል ህዝቡን መደገፍ ቢገባም ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ያለመተባበር፣ በቂ ያልሆነ የገንዘብ ድጋፍ፣ የደህንነት ስጋቶች፣ የወጪ መጨመር፣

የኮንትራክተሮች በቂ ያልሆነ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የዲዛይን ክለሳዎችን ለፕሮጀክቶች አፈፃፀም መጓተት ወይም በተቀመጠላቸው ጊዜ ላለመጠናቀቃቸው እንደ ተግዳሮት አንስተዋል፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በውሃ አስተዳደር ውስጥ የተቋማት ሚና እና መስተጋብር በእንዳለው ጅባት እና ሌሎች፣2024 የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በውሃ ሀብት አስተዳደር ላይ የተስተዋሉ ውሱንነቶች የተዋንያን (actors) ግልጽ ሚናና ኃላፊነት አለመኖር፣ ትርጉም ያለው ያልተማከለ አስተዳደር አለመኖር፣ በፖሊሲ ልማት ውስጥ ቁልፍ ተዋናዮች ተሳትፎ ውስንነት፣ በተቋማቱ መካከል ያለው ቅንጅት እና የማስፈጸሚያ ዘዴዎች አለመኖር፤ የግልጽነት እጦት፤በቂ ያልሆነ ስልጠና እና የአቅም ግንባታ፣የመሠረተ ልማት ጥገና ቸልተኝነት፣ሪፖርቶችን ማጭበርበር፣ሙስና እና የመልካም አስተዳደር እጦት ይገኙበታል፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እና የፕሮጀክት አፈጻጸምን ወቅታዊና ቀልጣፋ ለማድረግ የተሻሻለ አስተዳደር፣ ስትራተጂክ ዕቅድ እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር እንደሚጠይቅ ጥናቱ ይመክራል፡፡

- የፕሮጀክቶች ጥራትና ዲዛይን አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን፣
- ለመስኖ ግንባታ (ፕሮጀክቶች) ተቋራጮችን (ድርጅቶችን) ህግን ተከትሎ የግንባታ ስራዎችን አለማስተላለፍ፣ላልተጠናቀቁ እና ላልተሠሩ ሥራዎችም ክፍያዎችን ማከናወን፣
- ለተቋራጮች (ድርጅቶች) የተሰጠውን ግንባታ የመከታተል እና የማስፈፀም ክፍተት፣ በቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገነቡ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው ያሉ አካላት የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣የልማት ተነሺዎች የካሳ አከፋፈል ሂደት ደካማ መሆን፣
- በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ በቂ ቁጥጥር አለማድረግ እና የግልጽነት እጦት ጥቅቶቹ ናቸው፡፡

ስለዚህ እነዚህና የመሳሰሉት ከፕሮጀክት አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ብልሹ አሰራሮች ለትክክለኛው ትግበራ የታሰቡ ገንዘቦችን ወደ ኪስ እያስገቡ ዝቅተኛ ጥራት ያለው ሥራ የሚሰሩና ጥራት የሌላቸው የፕሮጀክት ግብቶችን የሚያቀርቡ ተቋራጮችን መጠቀም፣የውሸት ሪፖርት ማቅረብ፣Ghost (የምናብ) ፕሮጀክቶችን መፍጠር፣እና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች ሊያስከትል ይችላል፡፡

## አስረጂ ናሙና 2፡- የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር የተያያዘ

*የሌሶቶ ሃይላንድስ የውሃ ፕሮጀክት (LHWP) በዓለም ላይ ካሉ ትላልቅ የውሃ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። እ.ኤ.አ. በ1986 የደቡብ አፍሪካ እና የሌሴቶ መንግስታት የተፈራረሙትን ስምምነት መሰረት በማድረግ ለደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ሜትሮፖሊታን ክልል የውሃ አቅርቦትን ለመጨመር እና የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በሌሴቶ ደጋማ ቦታዎች የሚገኙ በርካታ ትላልቅ ግድቦች እና ዋሻዎች ያማከለ ስራ ነበር። የሁሉም ደረጃዎች አጠቃላይ የሚጠበቀው ወጪ 8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው። በምላሹም ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ከውኃ ሽያጭ እንዲሁም ከውኃ ኤሌክትሪክ ኃይል ከፍተኛ የሮያሊቲ ክፍያ እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። የፕሮጀክቱ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገው በአለም ባንክ፣ በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ በደቡብ አፍሪካ ልማት ባንክ፣ ባንኬ ናሽናል ዴ ፓሪስ፣ ክሬዲት ሊዮኔይስ፣ ድሬስነር እና በርካታ የኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲዎች እንዲሁም የሌሴቶ መንግስትን ጨምሮ በተለያዩ የአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ነው።*

*የሌሶቶ ሃይላንድስ የውሃ ፕሮጀክት LHWP በሌሴቶ ሃይላንድስ ልማት ባለስልጣን (LHDA) ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግ ድርጅት ነው። እ.ኤ.አ. በ1993 በተደረገ የውስጥ ኦዲት በተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትር ትዕዛዝ፣ LHDA ዋና ስራ አስፈፃሚ በሰጡት መግለጫዎች ላይ ህጋዊ ጥሰቶች ተገኝተዋል። በሌሴቶ ባለስልጣናት የተደረገ ተጨማሪ ምርመራ በስዊዘርላንድ እና በደቡብ አፍሪካ ለዋና ስራ አስፈፃሚ የባንክ ሂሳቦች መገኘቱን እና ለእነዚያ አካውንቶች ህገ-ወጥ ክፍያዎች በአለም አቀፍ የግንባታ ድርጅቶች ተወካዮች በኩል ክፍያ መፈፀማቸውን ማስረጃዎች ተገኙ። በጨረታው ወቅት በአጠቃላይ ከ6 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ጉቦ ተከፍሏል። እ.ኤ.አ. በ 2002 ዋና ሥራ አስፈፃሚው በ 11 የጉቦ እና ሁለት የማጭበርበር ክሶች ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በሌሴቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 18 ዓመት እስራት ተፈርዶበታል (በኋላ ይግባኝ ወደ 15 ዓመት ተቀነሰ)።*

*ዋና ስራ አስፈፃሚውን ጉቦ የሰጡ አማላጆችም ተከሰው በርካታ የቅጣት ውሳኔዎች ተላልፍል። በተጨማሪም ሶስት የግንባታ ድርጅቶች ምርመራ ተደርጎባቸው ለዋና ስራ አስፈፃሚው በአማላጆች ጉቦ በመክፈል በሚል ተፈርዶባቸዋል። በአጠቃላይ 19 የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የተሳተፉ ሲሆን የአለም ባንክ ሁለት ኩባንያዎች በባንክ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ለበርካታ አመታት እንዳይወዳደሩ ከልክሏል።*

*በዚህ የከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳይ ሶስት ጉዳዮች አስፈላጊ ነበሩ፡፡ አንደኛው በተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትሩ የታዘዘው የመጀመሪያ ኦዲት ሲሆን ለተጨማሪ ምርመራ ያደረጋቸው በርካታ ግድፈቶች መገኘቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሁለተኛ፣ የስዊዘርላንድ መንግሥት የዋና ሥራ አስፈጻሚ የባንክ ሂሳቦችን ምስጢራዊነት ለማንሳት ተስማምቷል፡፡ እና በሶስተኛ ደረጃ፣ የሌሴቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለም አቀፍ የጉቦ ኔትወርክን በአማላጆች ለመፍታት ያሳየው ጽናት ወሳኝ ነበር– በደቡብ አፍሪካ መንግስት እና በአውሮፓ ህብረት ፀረ-ማጭበርበር ኤጀንሲ ኦላፍ በተሳካ ሁኔታ የተከተለው ጥረት ነበር፡፡*

**Source (ምንጭ):** UNDP, 2011, Fighting Corruption in the water Sector Methods, Tools and Good Practices, New York, NY 10017, USA.

**የመወያያ ጥያቄዎችን**

<u>ከላይ ያለውን አስረጂ ናሙና አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኃላ በቡድናችሁ ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች ላይ በጥልቀት ከተወያያችሁ በኃላ ለተሳታፊዎቹ አቅርቡ፡፡</u>

- ✓ ከዚህ የናሙና አስረጂ ምን ተረዳችሁ?
- ✓ በዚህ የአስረጂ ናሙና ውስጥ የተስተዋሉ የሙስን ወንጀሎች ምንምንድናቸው?
- ✓ በዚህ የአስረጂ ናሙና ውስጥ የተስተዋሉ የሙስን ወንጀሎች በእናንተ ሚ/መ/ቤት የሚስተዋሉ ናቸውን? ከተስተዋሉ መገለጫዎቹስ ምን ምንድናቸው?
- ✓ በአሰረጂ ናሙናው የተስተዋሉ የሙስና ተግባራት የሚያስከትለው ጉዳት እንዴ ታያላችሁ? በምሳሌ ይደገፍ፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች ያሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድናችሁ ተወያዩና የውይይታችሁን ውጤት ለተሳታፊዎቹ አጋሩ፡፡</u>

1. የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍን ለሙስና ተጋላጭ ያደረጉት ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው ብላቸሁ ታስባላችሁ?
2. በዚህ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ዓይነቶች  የትኞቹ ናቸው? መገለጫቸውስ?

**የማጠቃለያ ሃሳብ**

በአጠቃላይ የመስኖና ቆላማ ልማት ሚኒስቴር ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነቱ ለግብርና ምርታማነት፣ለምግብ ዋስትና እና ለዘላቂ ልማት ከፍተኛ አደጋ አለው፡፡ በቂ ቁጥጥር አለማድረግ፣ደካማ የግዥ አሰራር እና የመልካም አስተዳደር ማዕቀፎች ለሙስና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሀብት አጠቃቀምን እና የፕሮጀክት ትግበራን ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፡ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች እና የመከላከያ ስልቶች

### 3.1 መግቢያ

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ጉዳቶቹን ለመረዳትና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.2 የምዕራፉ ዓላማ

ከስልጠና በኋላ ሰልጣኞቹ፡-

- ✓ በዘርፉ ያሉ ሙስና ና ብልሹአሰራረሮች የሚያደርሱትን ጉዳቶች ይረዳሉ፣ይተነትናሉ፣
- ✓ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- ✓ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
- ✓ በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፣
- ✓ የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
- ✓ በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

### 3.3ስልጠናው የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ፤

ስልጠናው 3፡00 ሰዓት ሊወስድ ይችላል፡፡

### 3.4የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ምን አይነት ጉዳቶችን ያስከትላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
3. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
4. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

### 3.5 በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች

በዘመናችን በተደጋጋሚ ከሚነገሩ፣ ከሚደመጡ በብዛትም ከሚፃፍባቸው የህዝብና መንግስት አንገብጋቢ የውይይት አጀንዳዎች መካከል አንዱ "ሙስና" ነው፡፡ ሙስና ለአንድ ሀገርና ህዝብ ህልውና ከፍተኛ ስጋት ነው፡፡ ሙስና በተንሰራፋበት ሥርዓት መልካም አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም፡፡ መልካም አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ይረጋገጣሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ሦስቱም የማይነጣጠሉ ወሣኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሙስና በኢትዮጵያ ከኑሮ ውድነትና ስራ አጥነት ቀጥሎ የአገር ደህንነት ስጋት መሆኑ በመንግስት ይፋ ሆኗል፡፡ ሙሰኝነት በሁሉም ዘርፎች ውስጥ ያለ ቢሆንም በጣም ጎልቶ የሚታያው ግን ለሀገራችን እድገት ወሳኝ በሆኑና መንግስት ከፍተኛ በጀት በሚመድብላቸው የኢኮኖሚው ዘርፎች ነው፡፡(https://www.lawethiopia.com/images/training_materials/Anticorruption%20law.pdf)

በመስኖ እና በቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የተለያዩ አስከፊ መዘዞችን ያስከትላሉ፣ በአካባቢ፣ በኢኮኖሚ እና በህብረተሰብ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ የበለጠ ደግሞ የሚከተሉትን ጉዳቶች ያስከትላሉ፡፡

1. **የኢኮኖሚዊ ጉዳቶች**

- ***የግብርና ምርታማነት መቀነስ***፦ የሃብት አላግባብ መመደብ በቂ መሠረተ ልማቶች እና የግብርና ግባዓቶች እንዳይኖሩ በማድረግ የሰብል ምርት እንዲቀንስ እና የምግብ ዋስትና እጦትን ያስከትላል፡፡ለመስኖ ፕሮጀክቶች የታቀደ ገንዘብ በደንብ ያልተገነቡ ወይም የተበላሹ መሠረተ ልማቶችን እንድገነቡም ያደርጋል፡፡
- **የገንዘብ ብክነት**፦ለወሳኝ ፕሮጀክቶች የታቀዱ ገንዘቦች ሲመዘበሩ ወይም አላግባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ ለመንግስት እና ለግብር ከፋዮች የገንዘብ ኪሳራ ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ሙስና በገንዘብ ምዝበራ ምክንያት በደንብ ያልተገነቡ የመስኖ አውታሮች እንዲፈጠሩ በማድረግ የገንዘብ ብክነትን ያስከትላል፡፡
- **በከተማ የምግብ ዋጋ መናር፡** አርሶ አደሩን በቂ እህል ካላመርተ እና ለገበያ ካላቀረበ በከተማ ለሚኖረው ነዋሪ በአቅርቦት እጦት ምክንያት የምግብ ዋጋ ንረትን በማባባስ በከተማ የኢኮኖሚ ቀውስ በመፍጠር የኢኮኖሚ መናጋት ሊከሰት ይችላል፡፡
- **ፍትሃዊ ያልሆነ የሃብት ስርጭት እንዳይኖር ያደርጋል**፦ ሙስና ጥቅማጥቅሞች ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ክልሎች እንድሆኑ በማድረግ ኢ-ፍትሃዊነትን ሊያባብስ ይችላል፡፡
- **የኢንቨስትመንት መጥፋት**፦ በብልሹ አሰራር ምክንያት መተማመን ማጣት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንቶችን በእርሻና በመሰረተ ልማት ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡
- **የድህነት መጨመር፦** በውጤታማ ባልሆነ መስኖ ላይ ጥገኛ የሆኑት አርሶ አደሮች በዝቅተኛ ምርታማነት እና በከፍተኛ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሊገጥማቸው ይችላል፡፡
-

2. **የአካባቢ ብክለትና ውድመት**

- **የውሃ እጥረት**፦ የመልካም አስተዳደር እጦት የውሃ ሃብትን ከመጠን በላይ መጠቀም፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ማሟጠጥ እና ስነ-ምህዳሮችን ሊጎዳ ይችላል፡፡
- **የአፈር መሸርሸር**፦ውጤታማ ያልሆነ የመስኖ አሠራር የአፈርን ጨዋማነት እና የአፈር መሸርሸርን ያስከትላል፣የመሬት ምርታማነትን ይቀንሳል፣

- **ብክለት**:-ጥራቱን ካልጠበቁና በጥሩ ሁኔታ ካልተያዙ ከመስኖ ግድቦች የሚወጣው ፍሳሽ ጎጂ ኬሚካሎችን ወደ አካባቢው የውሃ አካላት በማስተላለፍ የብዝሃ ህይወትን ይጎዳል።የውሃ ጥራትን ለመጠበቅ የታቀዱ ገንዘቦች ሊነጠቁ ይችላሉ። ይህም የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ወደሚያበላሹ የመሰረተ ልማት ውድቀቶች ይመራሉ።

3. **ማህበራዊ ቀውስ**

- **ኢ-እኩልነት እና ኢ-ፍትሃዊነትን መስፋፋት**: ሙስና ብዙውን ጊዜ በቁጥር ትንሽ የሆኑትን ልሂቃንን ይጠቅማል፣ ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች ያባብሳል። በመሆኑም አርሶ አደሮች ውሃ ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይችላሉ፣ ይህም የሀብት እኩልነት መብትን ይጎዳል።

- **የሀብት ግጭት**:- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለሚሄደው የውሃ ሀብት ፉክክር በተለያዩ የግብርና ዘርፎች ወይም ማህበረሰቦች መካከል ግጭትን ያስከትላል።
- **የእምነት መሸርሸር**:- ባለሥልጣናቱ ለግል ጥቅማጥቅሞች ወይም ጉቦ በመቀበል ለሚፈልጓቸው ድርጅቶች ፕሮጀክቶችን ሊሰጡ ይችላሉ። ይህም ህዝቡ በመንግስት እና በተቋማት ላይ ያለው እምነት እየቀነሰ የዜጎች ግንኙነት እና ትብብር እንዲቀንስ ያደርጋል፣ማህበረሰቡን በልማት ውጥኖች ውስጥም ለማሳተፍ አስቸጋሪ እና ተስፋ እንዲቆርጡያደርጋል። ሙስና እኩል ያልሆነ የገንዘብ ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ ከሙስና ባለስልጣኖች ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተወሰኑ ክልሎችን ወይም ባለድርሻ አካላትን በመደገፍ በማህበረሰቡ መካከል አለመግባባት ይፈጥራል። በዚህም ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት በማጣት በመካከላቸው ክፍተት ይፈጥራል።

4. **የጤና ተጽእኖዎች**

- **የውሃ ወለድ በሽታዎች**:-ያደርጋል።ሙስና የውሃ ሀብትን በአግባቡ አለመተዳደርን ያስከትላል።በዚህም ምክንያት የመጠጥ ውሃ ከግብርና ፍሳሽ መበከል ወይም በቂ የንፅህና አጠባበቅ ጉድለት ያስከትላል። በመሆኑም ደካማ የመስኖ አያያዝ የውሃ ወለድ በሽታን ይፈጥራል ይህም እንደ ወባ እና ኮሌራ ያሉ በሽታዎችን በአከባቢው ማህበረሰብ ላይ እንዲከሰቱ ፡
- **የተመጣጠነ የምግብ እጥረት**:-የግብርና ምርት መቀነስ የምግብ ዋስትና እጦትን ያስከትላል፣ በተለይም በህዝቦች ላይ ለምግብ እጥረት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

5. **የረጅም ጊዜ ዘላቂነት ጉዳዮች**

- **የመሰረተ ልማት ውድመት**፡-ሙስና የመስኖ አውታሮችን በበቂ ሁኔታ እንዳይንከባከብ እና ወቅታዊ ጥገና እንዳይደረግ ስለሚያደርግ ውሎ አድሮ ውድቀቱን እና የጥገና ወጪን ይጨምራል፡፡
- **የፈጠራ እጦት**፡- በብልሹ አሰራር ምክንያት የሚዘዋወሩት ግብዓቶች ዘመናዊና ዘላቂ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን ይከላከላል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች**

በሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ በቡድናችሁ ተወያዩና የውይይታችሁን ውጤት ለተሳታፊዎቹ አጋሩ፡፡

1. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች ምን ጉዳት ያስከትላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?፤፤
2. በዚህ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናዎች በገጠር ልማትና በግብርና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው የአጭርና የረዥም ጊዜ ጉዳቶች ምንድን ናቸው?
3. በዚህ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ሕዝቡ በመንግሥት ተቋማት ላይ ያለውን እምነትና ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል ብላችሁ ታስባላችሁ?

**የማጠቃላያ ሃሳብ**

በመስኖ እና በቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት አስተዳደር የሚስተዋለው ሙስና የግብርና ምርታማነትን፣ የአካባቢን ዘላቂነት እና የማህበራዊ ፍትሃዊነትን ሊያዳክም የሚችል ከፍተኛ ተጋላጭነቶችን ይፈጥራል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሙስና ውጤቶች በተለያዩ ጎጂ መንገዶች ይገለጣሉ፡፡ ለምሳሌ የሀብት አመዳደብ፣ ኢ-እኩልነት መጨመር፣አካባቢ መራቆት፣የህዝብ አመኔታ መቀነስ፣ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ እና የመሳሰሉትን ጉዳቶች ሊያመጣ ይችላል ይችላል፡፡ እነዚህን ተጋላጭነቶች ለመፍታት ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና የህብረተሰቡን በመስኖ እና በቆላማ አካባቢ አስተዳደር ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የባለድርሻ አካላት ለታማኝነት እና ለሥነ ምግባር አስተዳደር ቅድሚያ በመስጠት የሙስና ችግሮችን በመቅረፍ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚጠቅም ፍትሃዊ የግብርና ስርዓትን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 3.6 በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ዘርፍ የሚፈፀሙ ሙስና የመከላከያ ስልቶች

### 3.6.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ስለዚህ የዘርፉ ሰራተኞች በሥነ ምግባር፣በታማኝነት አስፈላጊነት እና በሙስና መዘዞች ላይ ያተኮሩ መደበኛ አውደ ጥናቶችን ላይ መሳተፍ፣ለብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ለመቀነስ በፕሮጀክት አስተዳደር፣ በጀት ማውጣት እና ግዥ ላይ ክህሎታቸውን በሚያሳድጉ ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ፣ በሙስና ምልክቶች፣ በሪፖርት አቀራረብ ዘዴዎች እና ግልጽነት አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤን ማዳበርና ለሌሎችም በማካፈል ሚኒስቴር መ/ቤቱን ከሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የፀዳ ማድረግ፡፡

### 3.6.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

- **ግልጽነት**

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሚኒስቴር መ/ቤት የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

ስለዚህ የዘርፉ ሰራተኞች ለምሳሌ ሐላፊዎች፤የመስኖ ፕሮጀክቶች አሰተዳደር መመሪዎች ፤ ግንባታ ላይ የሚሳተፉ አካላት ፤ የፕሮጀክቱ አዋጨነት ወ.ዘ.ተ ሥራቸውን ለስራ ባልደረቦቻቸው እና በሕዝብ መፈተሽ እንዲችሉ በግልጽ በመሥራት፣ለድርጊታቸው እና ለውሳኔዎቻቸው ተጠያቂ በመሆን፣ ፕሮጀክቶችን፣ በጀቶችን እና ውጤቶችን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ ማወቅና በማካፈል፣በንግግራቸው ግልጽ በመሆን ሕዝቡ በሚኒስቴሩ ላይ እምነት እንዲያድርባቸው አስተዋጽኦ በማድረግ ሙስናን ይከላከላሉ፡፡

- **ተጠያቂነት**

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

ስለሆነም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች ሁሉም እርምጃዎች ከህግ እና ከስነምግባር ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን በማረጋገጥ የሚ/መ/ቤቱን ፕሮቶኮሎች እና ደንቦችን በመከተል፣በፕሮጀክት አተገባበር፣ በፋይናንሺያል ወጪዎች እና በውጤቶች ላይ መደበኛ ሪፖርቶችን በማቅረብ፣ መረጃን በተቆጣጣሪዎች እና በህዝብ እንዲገመገም በማድረግ፣የፕሮጀክቶችን መደበኛ ክትትል በማድረግ የተዛቡ ጉድለቶችን በመለየት እና ሪፖርት

በማድረግ በፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል ሀላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

### 3.6.3 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

ሁሉም ሰራተኞች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የታማኝነት ባህልን በማጎልበት እንደ ታማኝነት፣ ፍትሃዊነት እና ግልጽነት ያሉ መርሆችን ማክበርና ማስከበር፣ስነ-ምግባር የጎደለውን ድረጊት ሪፖርት በማድረግ ከሙስና የፀዳ ሚኒስተር መ/ቤት ለመፍጠር የዜጊነት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

### 3.6.4 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ

ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

የንብረት ምዝገባ ሰራተኞች ቦታቸውን ለግል ጥቅማቸው አላግባብ እንዳይጠቀሙበት በማድረግ የፍላጎት ግጭቶችን ለመለየት ያስችላል፣በሠራተኛው የፋይናንስ ሁኔታ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ለመከታተል ይረዳል፣ ይህም ብልሹ አሰራሮችን ሊያመለክቱ የሚችሉ ልዩነቶችን ለመለየት ቀላል ያደርገዋል፣በሠራተኞች መካከል የታማኝነት እና የተጠያቂነት ባህልን ያዳብራል፣በሕዝብ አገልግሎት ውስጥ የሥነ-ምግባር ባህሪን አስፈላጊነት ስለሚያጠናክር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች በየጊዜው ንብረታቸውን በማስመዝገብ እና በማሳወቅ ሙስናን ለመከላከል ግንባር ቀደም ሚና መጫወትአለባቸው፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ሰራተኞች ያስመዘገቡት ሐብት ትክክለኛነቱን የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማጣራት፤ ማረጋገጥ እና ከተመዘገበው ሰነድ ጋር በማመሳከር የተጭበረበረ ሆኖ ከተገኘ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፡፡

### 3.6.5 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች ለጥቅም ግጭቶች በተመለከተ የራሳቸውን ሁኔታዎች በየጊዜው መገምገም፣ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን ለተቆጣጣሪዎቻቸው ወይም ለተሰየሙ የስነ-ምግባር ኃላፊዎች ማሳወቅ፣የዘርፉን የግጭት ፖሊሲዎችን/ህጎች ማወቅና በተግበር፣ውሳኔዎችን ከመወሰናቸው በፊት የግል ፍላጎታቸው ታማኝነትን ሊያበላሹ እንደማችሉ ማሰብ እና የመሳሰሉትን ተግባራት በመተግበር ብልሹ አሰራሮችን መዋጋት አለባቸው፡፡

### 3.6.6 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 3.6.7 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋሙ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፦

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣

- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት።

በመስኖ እና ቆላማ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ ያሉ አመራሮች ሙስናን በሁሉም ተግባራት ውስጥ የስነምግባርን አስፈላጊነት በማጉላት በአገልግሎት ውስጥ ያለውን የታማኝነት ራዕይ መግለፅ እና ማሳወቅ፣የፀረ-ሙስና ርምጃዎች በሚኒስቴሩ ስትራቴጂክ ዕቅዶችና ዓላማዎች ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፣ድምፃቸው እንዲሰማ እና ግልጽነት እንዲሰፍን የአካባቢ ማህበረሰቦችን በፕሮጀክት እቅድ እና ትግበራ በንቃት ማሳተፍ፣የሥነ ምግባር ደረጃዎችን/መለኪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የፕሮጀክት አፈፃፀምን እና የሰራተኞችን ምግባር ለመቆጣጠር ስርዓቶችን መዘርጋት፣ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና አደጋዎችን በመለየት በፍጥነት ለመፍታት የውስጥ እና የውጭ ኦዲቶችን ማመቻቸት፣በስነምግባር የታነፁ እና ለፀረ-ሙስና ጥረቶች አስተዋፅኦ ላደረጉ ሰራተኞች እውቅና መስጠት እና ሽልማት መስጠት እና የመሳሰሉትን ተግባራት በማከናወን ሙስናን ለመከላከል ሚናቸውን መወጣት አለባቸው።

### 3.6.8 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል። እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል።

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ሰራተኞች ሙስናን መዋጋት የሚችሉት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተለዩ ተግባራት ማለትም፦የፕሮጀክት ግቦችን ለመወያየት እና ግብረ መልስ ለመሰብሰብ ከማህበረሰብ አባላት ጋር መደበኛ ስብሰባዎችን ማደራጀት ፣ እምነትን እና ግልፅነትን ማጎልበት፣የፕሮጀክት አተገባበርን ለመከታተል የሚያግዙ የሀገር ውስጥ ተሚጋቾችን በመለየትና እና በመደገፍ ማናቸውንም ጥሰቶች ሪፖርት ማድረግ፣ሙስናን በመዋጋት ላይ ያተኮሩ በአካባቢያዊ አውታረ መረቦች ውስጥ መሳተፍ፣ ልምዶችን እና ስልቶችን ለስራ ባልደረቦቻቸው በመጋራት አለባቸው።

**አስረጂ ናሙና 3፦ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ሆኖ ሙስናን መከላከል**

*የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም በ2011 ባዘጋጀው የውሃ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ሙስና፣ የመዋጊያ ዘዴዎች፣ መሳሪያዎች እና ጥሩ ልምዶች ባዘጋጀው ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ሙስናን ለመካላከል እና ለመቀነስ የተለያዩ ሐገራትን ልምድ አስቀምጧል። አንደ ምሳሌም በፈረንሳይ በሁለቱ የፈረንሳይ የውሃ ኮንትራተሮች ላይ የተከሰውን ሙስና ከህግ አስከባሪው ጋር በጋራ በመሆን ኮንትራተሮቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲውሰድ አደርጉል።*

*ሁለቱ የፈረንሳይ የውሃ ኢንተርናሽናል በፈረንሳይ የውሃ ኮንትራቶችን ለማግኘት ጉቦ በመክፈል በወንጀል ተይዘው ተፈርደባቸዋል። እ.ኤ.አ. በ 1996 ግሬኖብል ውስጥ የቀድሞ ከንቲባ እና የመንግስት ሚኒስትር እና የሊዮኔይስ ዴስ ኤውክስ ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ (አሁን ሱዌዝ-ሊዮኔዝ ዴስ ኦውስ) የውሃ ኮንትራቱን በመቀበል እና ጉቦ በመስጠት የእስር ቅጣት ተፈርደባቸዋል። በአንጎሉሜ የቀድሞ ከንቲባ በ1997 ለሁለት አመታት ታስረዋል፣ ሌላ ሁለት አመት ታግዶ ነበር፣ ጌኔራሌ ዴስ ኤውንን ጨምሮ ኮንትራት ለመፈፀም ከሚጫረቱ ኩባንያዎች ጉቦ በመቀበል። የጄኔራሌ ዴስ ኤውክስ ሥራ አስፈፃሚዎች የውሃውን ስምምነት ለማግኘት ለሴንት ዴኒስ (ኢሌ ዴ ላ ሪዩን) ከንቲባ ጉቦ በመስጠት ተፈርደባቸዋል። እነዚሁ ቡድኖች-ሱዌዝ-ሊዮኔዝ እና ቪቬንዲ ከBouygues ጋር በመሆን ፈረንሳይ ውስጥ በግንባታ ክፍሎቻቸው ውስጥ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ምርመራ ተካሂደዋል። ይህም 'የህዝብ ገንዘብን ያለአግባብ ለመበዝበዝ የተስማማበት ስርዓት' ተብሎ በተገለጸው ቅሌት ነው. ኩባንያዎቹ በ ኢሌ-ዴ የፈረንሳይ ክልል (በፓሪስ አካባቢ) በ1989 እና 1996 መካከል 2.8 ቢሊዮን ፍራንክ (500ሚሊየን ዶላር ገደማ) የሚያወጡ ውሎች በሦስቱ ቡድኖች ተጋርተዋል።*

**Source (ምንጭ):** UNDP, 2011, Fighting Corruption in the water Sector Methods, Tools and Good Practices, New York, NY 10017, USA.

### 3.6.9 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው

የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ሰራተኞች ሙስናን ለመከላከል ደህንነታቸው እና ሚስጥራዊነታቸውን በተጠበቀ መልኩ የሞባይል መተግበሪያዎችን በመጠቀም ስነ-ምግባር የጎደለው ባህሪ ወይም የሙስና ወንጀልን ሪፖርት ማድረግ ፣በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ግብረመልስ የሚሰጡበት እና ስለ ሙስና ጉዳዮች ስጋቶችን የሚያነሱበት ዲጂታል መድረኮች ላይ መሳተፍ፣በታማኝነት እና በፀረ-ሙስና ልማዶች ላይ ያተኮሩ ኢ-ለርኒግ ላይ መሳተፍ እና ስለፕሮጀክቶች መረጃ ለመለዋወጥ እና በክትትል ውስጥ የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማበረታታት ማህበራዊ ሚዲያን መጠቀም ይችላሉ፡፡

**አስረጂ ናሙና 4፡-ሙስናን ለመከላከል ቴክኖሎጂ ያለው ሚና**

እ.ኤ.አ. እስከ 1985 ድረስ በባንግላዲሽ ውስጥ በባሪንድ ክልል ውስጥ የቱቦ መስኖ የተለመደ አልነበረም። በከፊል በረሃማ የሐገሪቱ አካባቢ ወስጥ ዝናብን መሰርት ያደረገ ሩዝ በዋና ሰብልነት ይመርት ነበር። በ1985 የአካባቢው ባለስልጣናት የከርሰ ምድር ውሃን ለመስኖ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ፕሮጀክት ቀርሶ ወደ ስራ አስገባ። ከጥቂት አመታት በኋላ የባሪንድ ሁለገብ ልማት ባለስልጣን (BMDA) ፕሮጀክቱን ተረከበ። ለፕሮጀክቱ ዲዛይን በባንግላዲሽ የከርሰ ምድር ውሃ ልማት ቀደም ሲል የነበሩት ተሞክሮዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ ክትትል ያደርግ ነበር። በፕሮጀክቱም የከርሰ ምድር ውሃን የመሳብ አቅምን ከከርሰ ምድር ውሃ የመሙላት አቅም በታች ላለማድረግ ተጠያቂነት ያለው ደንብ ትልቁ ፈተና እንደነበር ይታወቃል። እ.ኤ.አ. በ1992 ባለስልጣኑ የቅድመ ክፍያ ሜትሮችን እና ስማርት ካርዶችን እንደ ፈጠራ ዘዴ በመጠቀም የከርሰ ምድር ውሃን ዘላቂ እና ተጠያቂነት ባለው መንገድ ለመቆጣጠር ዘዴ ፈጠረ።

በቅድሚያ የተከፈሉ ሜትሮች ቀስ በቀስ በእያንዳንዱ የባሪንድ ፕሮጀክት በተቆፈሩት ቱቦዎች ላይ እንዲተከሉ ተደርገዋል። ቀደም ሲል ከተከፈለ ቆጣሪ ጋር የተገናኙ ጉድጓዶችን ለማብራት(ለመጠቀም) ገበሬዎች ስማርት ካርድን ከአንባቢው ጋር ማስቀመጥ አለባቸው። እያንዳንዱ ገበሬ የራሱን ካርድ በመግዛት በሽያጭ ማሽኖች መጫን ይችላል። ዋጋው በእያንዳንዱ የፓምፕ (የውሃ መሳብ) ሰዓት ይሰላል እና ቆጣሪውም የኤሌክትሪክ ክፍያን፣ የኦፕሬተሩን ደመወዝ፣ የጥገና እና የጥገና ወጪዎችን እና የመነሻ ኢንቨስትመንትን ያካትታል።

በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ የገበሬዎች የቧንቧ ጉድጓድ ለመቆፈር ሲፈልጉ ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ያስገባሉ፡፡ የፕሮጀክቱ ውሃው የሚቀርበው ጉድጓድ ያለበት ቦታ ቢያንስ 2,500 ጫማ ርቀት ካለበት ጥልቅ ቱቦ ክልል ውሰጥ ሲገኝ ብቻ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡ በግምት 3,000 የአሜሪካ ዶላር በገበሬዎች እንደ ቅደመ ክፍያ የሚከፈል ሲሆን ቀሪው የመነሻ ኢንቨስትመንት የሚገኘው በአሞርቴሽን ሂደት ነው፡፡ በትክክል የትዕዛዝ ቦታው የተስተካከል፣የተዘረጋ የቧንቧ መስመር ላላቸው ጉድጓዶች፣ የትዕዛዝ ቦታ ከ 40ha በላይ መሆን አይችልም፡፡ እንደዚህ አይነት የውሃ ቆጣቢ የቧንቧ መስመር ስርዓት ለሌላቸው ጉድጓዶች፣ የትዕዛዝ ቦታ ከ 32ha በላይ መሆን አይችልም፡፡

የጉድጓዱ ጥግግት እና የቦታ ውስንነት ቢኖርም፣ የውሃ አርሶ አደሮች በስማርት ካርዳቸው የሚቀዳው ከፍተኛ ገደብ የለም፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የገበሬዎች የፋይናንስ አቅም የውሃ አጠቃቀምን ይገድባል፡፡ አርሶ አደሮች አብዛኛውን ጊዜ በእርሻ ወቅት ካርዳቸውን ብዙ ጊዜ መሙላት አለባቸው ምክንያቱም ለመስኖ ተራ ከሚያስፈልገው በላይ ውሃ ለመግዛት የሚያስችል በቂ ገንዘብ ስለሌላቸው፡፡

የባሪንድ ፕሮጀክት የቁጥጥር ስርዓት የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀምን ግልፅ እና ከሙስና የፀዳ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ነው፡፡ ስራዓቱም የዘርፍ ተዋንያንን ተጠያቂ ለማድረግ አዲስ መፍትሄ ነው፡፡ ከሌሎች የመስኖ አውታሮች በተቃራኒ ውሃው በድምጽ መጠን ይከፈላል እና ክፍያዎች የሚከናወኑት በግለሰቦች መካከል የገንዘብ ልውውጥ ሳይኖር ነው፡፡ በሽያጭ ማሽኖች ላይ ያለው አውቶማቲክ ክፍያ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ዋጋ እንደሚከፍል እና መደበኛ ያልሆኑ ክፍያዎችን አደጋን ቀንሷል፡፡ ከባዶ በመጀመር በምዝገባ ሂደቱ ወቅት ማጭበርበርን በአብዛኛው ማስቀረት ተችሏል፡፡

በባሪንድ ያለው የከርሰ ምድር ውሃ የመስኖ ፕሮጀክት ቴክኖሎጂን መጠቀም ሙስን አደጋዎችን በመቀነሱ ረገድ የሚጫወተውን ሚና ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ነገር ግን BMDA በግሉ ዘርፍ ላይ የሚደርጉ የምስኖ ቱቦ ቁፋሮ ላይ ያለው ቁጥጥር ውስን በመሆኑ ምክንያት፣ በባሪንድ ክልል የከርሰ ምድር ውሃ አጠቃቀም ዘላቂነት ሙሉ በሙሉ ማረጋገጥ አይችልም፡፡

**Source (ምንጭ):** UNDP, 2011, Fighting Corruption in the Water Sector Methods, Tools and Good Practices, New York, NY 10017, USA.

በአጠቃላይ መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ዘጠኝ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

በመሆኑም ዘርፉ ሙስናን ለመከላከል ጠንካራ የተጠያቂነት ዘዴዎችን መዘርጋት፣ የበጀት አወጣጥ እና የግዥ ሂደቶችን ግልፅነት ማሳደግ እና የመንግስት እንቅስቃሴዎችን በመከታተል ረገድ የዜጎችን ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር እና የታማኝነት ባህልን ማሳደግ ሀብቱን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋልን በማረጋገጥ በመጨረሻም በዚህ ወሳኝ ዘርፍ ላይ የተመሰረቱ አርሶ አደሮችንና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እና ብልሹ አሰራሮችን በመቅረፍ ሚኒስቴሩ የተጣለበትን ተልዕኮ በተሻለ ሁኔታ በመወጣት ለክልሉ ሁለንተናዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

<u>ከላይ ያለውን አስረጂ ናሙና አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኃላ በቡድናችሁ ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች ላይ በጥልቀት ከተወያያችሁ በኃላ ለተሳታፊዎቹ አቅርቡ፡፡</u>

- ✓ ከአስረጂ ናሙናው ምን ተገነዘባችሁ?

- ✓ በአስረጂ ናሙና ውስጥ የተገለፁት የሙስና ወንጀሎች በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ይንፀባረቃሉ? ካሉ በምን ይገለፃሉ? ለመከላከልስ ምን ምን እርምጃዎች ተወሰደዋል?
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ቴክኖሎጂ መጠቀም ሙስናን ይቀንሳል በላችሁ ታስባላችሁ?
- ✓ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ዘርፍ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሙስናን ለመከላከል የተደረጉ ሙከራዎች አሉ? በምሳሌ አሰደግፋችሁ አብራሩ፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡</u>

1. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኂቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
2. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂ መካከል በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
4. በዚህ ስልጠና ካያችኂቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

### የማጠቃለያ ሀሳብ

በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ሙስናን መዋጋት ዘላቂ የግብርና አሰራርን፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን እና አጠቃላይ የስነ-ምህዳርን ጤና ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ውጤታማ ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡ ለፕሮጀክት እቅድ ማውጣት፣ የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ እና ትግበራ ላይ ግልፅ ሂደቶችን መተግበር፣መደበኛ ኦዲት ማድረግ፣የአካባቢ ማህበረሰቦችን በውሳኔ ሰጪነት ማሳተፍ፣ሙስናን ለመከላከል ጠንካራ የህግ ድንጋጌዎችና የማስፈጸሚያ ዘዴዎች መዘርጋት እና የመሳሰሉት መተግበር አለባቸው፡፡

## ማጠቃለያ

በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ያሉ ሙስናና ብልሹ ተግባራት ላይ የስልጠናው ሞጁል የስነምግባር ጉድሎቶችን እና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ወሳኝ ግብአት ሆኖ ያገለግላል። ተሳታፊዎች ስለ ሙስና ምንነት እና ተፅእኖ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ እነዚህን ተግባራት እንዲያውቁ፣ እንዲከላከሉ እና እንዲዋጉ ያደርጋቸዋል። በተለይም ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ በሆኑ ክልሎች እና በውሃ እጥረት ምክንያት የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የመስኖ እና የቆላማ አካባቢዎች ወሳኝ ናቸው። ሙስና እነዚህን ዓላማዎች ያዳክማል፣ ይህም ወደ የሀብት ምዝበራ የህዝብ አመኔታ እንዲቀንስ እና በማህበረሰብ ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ያስከትላል። ስለዚህ ጠንካራ የመከላከል ስልቶችን መተግበር የቁጥጥር ግዴታ ብቻ ሳይሆን የሞራልም ግዴታ ነው።

ይህ ሞጁል በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የታማኝነት ባህልን በማጎልበት የግልጽነት፣ የተጠያቂነት እና የስነምግባር አስፈላጊነትን ያጎላል። የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ፣ የአስተዳደር ማፅቀፎችን በማሳደግ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሥነ ምግባራዊ ተግባራት የሚዳብሩበት፣ ሙስናን በዘዴ የሚፈታበትን ሁኔታ መፍጠር ያስችላል። ተሳታፊዎች ይህንን ስልጠና ሲያጠናቅቁ እውቀትን ብቻ ሳይሆን በሚኒስቴር መ/ቤታቸው እና በማህበረሰቡ ውስጥ መልካም ስነምግባርን የማሻሻል ሀላፊነትም በመወጣት በጋራ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ሀብቱን በአግባቡ በመምራት ሁሉንም ተጠቃሚ የማድረግ ሀላፊነትም እንዳለባቸው ግንዛቤን ይሰጣቸዋል።

በአጠቃላይ የፀረ ሙስና ትግሉ ቀጣይነት ያለው ሲሆን ይህ የስልጠና ሞጁል የበለጠ ግልፅ እና ፍትሃዊ የሆነ የወደፊት ጊዜ ለመገንባት ወሳኝ እርምጃ ነው።የተማሩትን በተግባር ላይ በማዋል ቁርጠኝነት፣ታማኝነት እና ተጠያቂነትን የስራ ባህላቸው በማድረግ ከሙስና የፀዳ የመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት እንዲገነቡ ብቃትን ይሰጣቸዋል።

# ራስን መገምገሚያ ቼክሊስት

1. ሙስናን መግለፅ እና የተለያዩ መገለጫዎችን(ለምሳሌ ጉቦ፣ ምዝበራ፣ ዘመድ አዝማድ) መለየት ችያለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

2. መስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ለሙስና እንዲጋለጥ የሚያደርጉ ምክንያቶችን አውቀቸዋለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

3. ሙስና በተለይ በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት ልማት ዘርፍ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ/ጉዳቶች እንደሚያሳድር ተረድቻለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

4. በመስኖ እና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የመዘግየት ምክንያታቸውን አውቃለው፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

5. በፕሮጀክት አስተዳደርና አተገባበር ላይ የተለመዱ የሙስና ምልክቶችን መለየት ችያለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

6. በስራ አካባቢዬ ውስጥ ያሉ ብልሹ አሰራሮችን ሊያመለክቱ የሚችሉ ቀይ ባንዲራዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

7. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች እና ሂደቶችን አውቀዋለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

   ለ. አይ ☐

8. ሙስና በሐገር ላይ ያለውን የህግ ማዕቀፍ እና በህዝብ አገልጋይነት ላይ ያለውን አንድምታ ተረድቻለሁ፡፡

   ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ☐

9. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ካሉ ሰራተኞች የሚጠበቁትን የስነምግባር ደረጃዎች መግለጽ ችያለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

10. በስራዬ ውስጥ ታማኝነትን እና ግልፅነትን የመጠበቅን አስፈላጊነት ተረድቻለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

11. የተጠረጠሩትን ሙስና ወይም ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ሪፖርት የማድረግ ሂደቶችን እና የሚደረጉ ጥበቃዎችን አውቃለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

12. ጠላፊዎችን እንዴት ማግኘት እንዳለብኝ ለእነሱን የሚደረገውን ጥበቃ ተረድቻለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

13. የአካባቢው ማህበረሰቦች እና ባለድርሻ አካላትን በፕሮጀክት እቅድ እና አፈፃፀም ላይ የመሳተፍን አስፈላጊነት ተረድቻለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

14. መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንዴት መስራት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡

ሀ. አዎ ☐

ለ. አይ ☐

## ዋቢ መፅሃፍት(ማጣቀሻዎች)

Corruption in the Water Sector" by the World Bank https:// www. taylorfrancis. com/chapters/edit/10.1201/9780203875438-28/corruption-transparency-water-sector-leary

Ethiopian Reporter https:// www. Ethiopian reporter. com/ 129149 https:// documents1.worldbank.org/curated/en/210171468024611636/pdf/699430PUB0Publ067869B09780821395318.pdf.

https://elearn.moe.gov.et/storage/sign%20language/Text%20Book/EthSL%20Gr.9-12%20final-PRIN%20submitted%20to%20MoE-6.6.2018/Grade%2012/unit%203.pdf

https://ema.gov.et/documents/20124/0/Final+mass+media+policy.pdf/aacbfae9-426a-0a6d-01fb-ad4b004b7819?t=1625814934766

https://heinonline.org/hol-cgi-bin/get_ pdf.cgi? handle= hein. journals/ brownjwa13 &section=28

https://www.africanews.com/2017/07/28/ethiopia-puts-37-people-before-court-over-high-level-corruption//

https://www.ema.gov.et/%E1%8B%A8%E1%88%98%E1%8C%88%E1%8A%93%E1%8A%B-%E1%89%A5%E1%8B%99%E1%8A%83%E1%8A%95 E1%8A%A0%E1%8B%8B%E1%8C%85

https://www.lawethiopia.com/images/training_materials/Anti-corruption%20law.pdf

https://www.lawethiopia.com/images/training_materials/Anti-corruption%20law.pdf

https://www.taylorfrancis.com/chapters/edit/10.4324/9781003179900-33/united-nations-office-drugs-crime%E2%80%94unodc-helen-canton

Index, C. P. (2018). Transparency international.https:// www. jstor. org/stable/ 27800285

Jibat, E., Senbeta, F., Zeleke, T., & Hagos, F. (2024). The role and interplay of institutions in water governance in the Central Rift Valley of Ethiopia. F1000Research, 12.

Peters, A. (2018). Corruption as a violation of international human rights. *European Journal of International Law*, *29*(4), 1251-1287.

Reif, L. C. (2020). Ombuds Institutions, Good Governance and Human Rights in Africa and Asia-Pacific. In *Ombuds Institutions, Good Governance and the International Human Rights System* (pp. 618-740). Brill Nijhoff.

Wells, J. (2015). Corruption in the construction of public infrastructure: Critical issues in project preparation. *U4 Issue*.

የዋልታቲቪ፡https://www.youtube.com/watch?v=cWJyFM8l08o፣የሪፖርተር ጋዜጣ፡https://www.ethiopianreporter.com/129149/) እና በፌደራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 የተደረገ ጥናትን፣2015 ሪፖርት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et